DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
DC MURIEL BOWSER, MAYOR

# ሁለትኛ ደረጃ መመሪያ
# ኮሮናቫይረስ 2019 (COVID-19)፣ ለተጋራ ትራንዚት መመሪያ
# (ለኪራይ ተሽከርካሪ፣ ታክሲ፣ እና ራይድሼር ተሽከርካሪዎች)

**በሁለተኛ ደረጃ ጊዜ፣ አስፈላጊ-ያልሆነ ራይድሼር እንደገና መጀመር ይችላል።** ለሁሉም አደጋን ለመቀነስ ህዝብ እና የንግድ ተቋማት አዳዲስ ባህሪያት እና ጥብቅ መከላከያዎችን እንዲላመዱ ይፈለጋሉ። ሁለተኛ ደረጃ ዉስጥ አገልግሎት ለመስጠት፣ **አሽከርካሪዎች፣ ሰራተኞች፣ ደንበኞች፣ እና ማህበረሰብ መካከል የCOVID-19 የተጋላጭነት አደጋን ለመቀነስ እንዲረዱ ቀጥሎ ያሉ እርምጃዎች ሥራ ላይ ሊዉሉ ይገባል።** ለተጨማሪ መረጃ፣ coronavirus.dc.gov/phasetwo ይጎብኙ።

የ COVID-19 ምልክቶችን እራሱ ላይ ያየ፣ ወይም በቅርብ ጊዜ ለ COVID-19 ተመርምሮ የተገኘበት ሰው ጋር የነበረ ማንኛዉም ግለሰብ፣ ሌሎችን የማጋለጥ አደጋ ምክንያት፣ ለ-ኪራይ፣ ታክሲ፣ ወይም ራይድሼር ተሽከርካሪ ላይ መስራት እንደሌለበት እባክዎ ያስታዉሱ። የ COVID-19 ምልክቶች የሚጨምሩት፥ትኩሳት (በግምት ወይም 100.4 ድግሪ ፋራናይት)፣ ቅዝቃዜ፣ ሳል፣ የእስትንፋስ እጥረት ወይም ለመተንፈስ መቸገር፣ ድካም፣ የጡንቻ ወይም የአካል ህመሞች፣ የራስ ህመም፣ አዲስ የጣዕም ወይም የሽታ ችሎታን ማጣት፣ የጉሮሮ ህመም፣ የአፊንጫ መታፈን ወይም የአፊንጫ ንፍጥ፣ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ፣ ተቅማጥ፣ ወይም የሌላ የጤንነት ስሜት ማጣት።

## አሽከርካሪዎች እና ደንበኞች በየቀኑ የመከላከል እምጃዎችን መለማመድ አለባቸው።

- **ከታመሙ** ወይም COVID-19 ያለበት ሰው ጋር በቅርብ ጊዜ ከተገናኙ **እቤት ይቆዩ።**
- ደንበኞች ከታመሙ፣ በጣም አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፣ ለ-ኪራይ፣ ታክሲ፣ ወይም ራይድሼር ተሽከርካሪን መጠቀም የለባቸዉም፣ እና የመኪና ማንሻ አማራጮችን መጠቀም የለባቸዉም።
- በተቻለ መጠን ከሌላ ሰዎች ቢያንስ 6 እርምጃ ርቀው ይቆዩ።
- አሽከርካሪዎች እና ደንበኞች በሁሉም ጊዜያት ፊት የሚሸፍን ልብስ መልበስ አለባቸው።
- በተቻለ መጠን ደንበኞች ሻንጣቸውን በራሳቸው መያዝ እና ንክኪ የሌለው የክፍያ አማራጮችን መጠቀም አለባቸው።
- በየተደጋጋሚ የእጅ ንፅህናን ይጠብቁ (በሳሙና እና ዉሃ ወይም አልኮል ያለው የእጅ ማሻሸት)።
    - የእጅ ንፅህናን ለመጠበቅ ወሳኝ ጊዜያት የሚጨምሩት፥
        - ምግብ ከመብላት በፊት፣
        - መፀዳጃ ቤት ከመጠቀም በኋላ፣
        - የፊት መሸፈኛ ልብስን ከመልበስ፣ መንካት፣ ወይም ማዉለቅ በፊት እና በኋላ፣
        - ከሥራ ፈረቃዎች እና ሥራ ዕረፍቶች በፊት እና በኋላ፣
        - ከጉዞ መካከል እና ገንዘብን ከመንካት/መለዋወጥ በኋላ፣
        - ጋዝ ከመሙላት በፊት እና በኋላ
        - የደንበኞች የግል ጓዞች መያዝ በኋላ፣ መተው የማይቻል ከሆነ፣ እና
        - አፍንጫዎን ከመንፋት፣ ሳል፣ ወይም ማስነጠስ በኋላ።
- አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪያቸው ዉስጥ ሶፍት መያዝ አለባቸው። ደንበኞች እና አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪው ዉስጥ ካሳሉ ወይም ካስነጠሱ አፋቸውን እና አፍንጫቸውን መሸፈን፣ የእጅ ንፅህናን መጠበቅ፣ እና ሶፍትን ቆሻሻ መጣያ ዉስጥ መጣል አለባቸው።
- ጓንቶች በተደጋጋሚ የሚሰሩ የሥራ ግዴታዎች መሰረት ሲታዘዙ ብቻ መለበስ አለባቸው።
- ደንበኞች የመከላከል እርምጃዎችን ለማክበር ፈቃደኛ ካልሆኑ፣እንዳስፈላጊነቱ፣ ይህንን ጉዳይ ለአስተዳደር፣ ለእርስዎ መተግበሪያ ራይድሼር ኩባኒያ፣ እና/ወይም ለባለስልጣኖቹ ሪፖርት ሊያደርጉ ይችላሉ።
- ለደህንነት ምክንያት፣ በግልፅ እየታመመ ላለው ደንበኛ የመጓጓዣ አገልግሎት ለመስጠት ጥሩ ስሜት የማይሰማዎት ከሆነ፣ የመጓጓዣ አገልግሎትን ላለመስጠት መምረጥ ይችላሉ። ይሁን እንጂ፣ በኩባኒያዎ ፖሊሲዎች፣ የአካባቢ፣ የስቴት፣ እና የፌዴራል ህግ ዉስጥ እንደተገለፀው በዘር፣ የብሄራዊ መነሻ፣ ወይም ሌሎች ምክንያት መሰረት ደንበኞች ላይ አድልዎ ማድረስ አይፈቀድም።

## የእሽከርካሪ እና የደንበኛ ደህንነትን ለማበረታታት ሰራተኛ/እሽከርካሪ ግምት ዉስጥ የሚያስገቡ ነገሮች

- የተጋራ መተላለፊያ አሰሪዎች የተደጋጋሚ የእጅ ንፅህናን በያንዳንዱ ተሽከርካሪ እና በስራ ጣቢያ ቢሮዎች እና የተለመዱ አካባቢዎች ዉስጥ ለመፍቀድ
- (ለምሳሌ፣ ሳሙና እና ዉሃ ወይም አልኮል-ያላቸው የእጅ ንፅህና መጠባበቂያዎች ቢያንስ በ60% አልኮል) ለአሽከርካሪዎች እና ሌሎች ሰራተኞች አቅርቦቶችን ማቅረብ አለባቸው።
- የተጋራ መተላለፊያ አሰሪዎች ለሰራተኞች አስፈላጊ የግል መከላከያ መሳሪያን (ለምሳሌ፣ የፊት እና አፍንጫ መሸፈኛዎች) እና የፊት መሸፈኛ ልብስን ማቅረብ አለባቸው።

- ተለዋዋጭ የሆኑ እና የማይቀጡ፣ እና የታመሙ ሰራተኞች ቤት እንዲቆዩ የሚፈቅዱ ከሥራ የመቅረት ፖሊሲዎችን ሥራ ላይ ማዋል። ከሥራ የመቅረት ፖሊሲዎች ቀጥሎ ያሉትን ለማስተናገድ ይመከራሉ፥
  - የ COVID-19 ምልክቶችን ሪፖርት የሚያደርጉ ሰራተኞች፣
  - ለ COVID-19 የተመረመሩ ሰራተኞች እና የምርመራ ዉጤቶቻቸው እየተጠባበቁ ያሉ፣
  - ለ COVID-19 ተመርምረው ፖዚቲቭ የሆኑ ሰራተኞች፣
  - ለ COVID-19 ተመርምሮ ፖዚቲቭ የሆነ ሰው ጋር የቅርብ ንክኪ ያላቸው ሰራተኞች፣
  - የትምህርት ቤት ወይም የልጅ እንክብካቤ መዝጊያዎች ካሉ ከልጆቻቸው ጋር ቤት መቆየት ያለባቸው፣ ወይም የታመሙ የቤተሰብ አባላትን የሚያንከባክቡ ሰራተኞች
- ሁለቱም የ DC የቤተሰብ እና የህክምና የመቅረት ፈቃድ ሕግ እና የ DC የህመም እና የደህንነት የመቅረት ፈቃድ ህግን ያሻሻለው እና ሙሉ በሙሉ አዲስ የመቅረት ፈቃድ ምድቦችን፣ እንደ የታወጀ የድንገተኛ ጊዜ መቅረት ዓይነት፣የፈጠረው ያሁኑ ህግ ወደ ጎን ማቆየት።
- በአዲስ የፌዴራል ህግ፣ የቤተሰቦች የመጀመሪያ የኮሮናቫይረስ ምላሽ ህግ (FFCRA) እና የህመም እረፍት ጋር የተያያዙ ሁሉም ሊተገበሩ የሚችሉ የዲስትሪክት ህጎች በኩል ስለሚቀርብ ከCOVID-ተያያዥ የሥራ መቅረትን ይወቁ እና ለሰራተኞችዎ ያሳዉቁ።
- የተጋራ የመተላለፊያ አሰሪዎች ፈረቃዎችን፣ የመጀመር ሰዓታትን፣ እና የእረፍት ሰዓታትን በተቻለ መጠን ማፈራረቅ አለባቸው።
- የተጋራ የመተላለፊያ አሰሪዎች፣ አሽከርካሪዎች እና ደንበኞች መካከል የቅርብ ንክኪ እና እስክሪብቶዎች እና የኤሌክትሮኒክ መፈረሚያ ፓዶችን የመሰሉ የቁሳቁሶች መጋራትን የሚገድቡ ወይም የሚያስወግዱ ከንክኪ-ነፃ ማስተላለፎችን የሚፈቅዱ እና ቅድሚያ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን እና የቴክኖሎጂ አማራጮችን መቅረፅ አለባቸው።
- የተጋራ የመተላለፊያ አሰሪዎች ሠራተኞቻቸውን ስለ COVID-19 ማስተማር አለባቸው። ለበለጠ መረጃ coronavirus.dc.gov ይመልከቱ።
- በተለይ የተጋራ መተላለፊያን የሚመለከት ተጨማሪ መረጃ፣ የበሽታ ቁጥጥር እና መከላከል ማእከላት (CDC) ድህረገፅን፥ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/organizations/rideshare-drivers-for-hire.html ይመልከቱ።

## ምልክቶችን ማጣራት እና መቆጣጠር

- የተጋራ የመተላለፊያ አሰሪዎች በየቀኑ፣ ፈረቃቸውን ሳይጀምሩ ወይም የሥራ ቦታን ከመግባታቸው በፊት፣ በስልክ ወይም በአካል ሰራተኞቻቸውን ማጣራት(ለምሳሌ፣ የምልክት መጠይቆች) አለባቸው።
  - ለ ***ማጣራት መሳሪያ መመሪያ***፣ coronavirus.dc.gov/healthguidance ይጎብኙ
- የተጋራ የመተላለፊያ አሰሪዎች ስለ ማጣራት ሂደቶች ለሠራተኞች እና ጎብኚዎች ለማሳወቅ ምልክቶችን የንግድ ቤት መግቢያ ላይ ማስቀመጥ አለባቸው።
- አንድ ሠራተኛ በስራ ቀን ማንኛዉም የ COVID-19 ምልክቶችን ካሳየ፣ ያ ግለሰብ ወዲያዉኑ ራሱን ለብቻ እንዲያወጣ፣ ተቆጣጣሪያቸውን/የራይድሼር ኩባኒያን እንዲያሳዉቅ እና ደንበኞችን ማጓጓዝ እንዲተው ወይም የሥራ ቦታውን ለቆ እንዲሄድ የሚያደርግ የተቀመጠ እቅድ መኖር አለበት።
- የተጋራ የመተላለፊያ አሰሪዎች የንክኪ አፈላለግን ለማመቻቸት ቢያንስ ለ 30 ቀናት ሥራው ዉስጥ ያሉ የግለሰቦች እና የደንበኞች መዝገብ መያዝ አለባቸው።

## የቅርበት ግንኙነትን ያስወግዱ እና የንክኪ ነጥቦችን ይቀንሱ።

- በአሽከርካሪው ደንበንኞች ፊት ለ ፊት ያለው የተጓዥ መቀመጫ ላይ እንዳይቀመጡ መከልከል።
- አሽከርካሪዎች የተጓዦች ቁጥርን ወደ 1 ሰው፣ ወይም ከአንድ ቤተሰብ ወደ መጡ ሰዎች መገደብ (ልዩ እይታዎች ሊጨምሩ የሚችሉት አስፈላጊ አብሮነት፣ እንደ የግል እንክብካቤ ረዳት).አለባቸው።
- አሽከርካሪ እና የተጓዥ መቀመጫዎች መካከል መከፋፈል ለመጠቀም ግምት ዉስጥ ያስገቡ።
- ከደንበኞች ጋር የቅርበት ግንኙነትን ያስወግዱ።
  - ከተሽከርካሪው ዉጭ ሲሆኑ ከደንበኞች ቢያንስ የ6 እርምጃ ርቀትን ይጠብቁ።
  - በመዉሰጃ እና ማድረሻ ጊዜ ደንበኞች የራሳቸውን የግል ሻንጣዎችን እና ጓዞችን በራሳቸው እንዲይዙ ለመጠየቅ ግምት ዉስጥ ያስገቡ። ይህ የማይቻል ከሆነ የእጅ ንፅህናን ይጠብቁ።
- በደንበኛ ማጓጓዣ ጊዜ ለመኪና ንፋስ እንደገና ዞሮ የመጣ አየር የመጠቀም አማራጭን ያስወግዱ፣አዲስ የዉጭ አየርን ለማስገባት የመኪናዉ ቬንትሌተሮችን ይጠቀሙ እና/ወይም መስታወቶችን ዝቅ ያድርጉ።
- እንደ ዉሃ ጠርሙዞች ወይም ጋዜጦች ያሉ ቁሳቁሶችን አይጋብዙ።
- ከማጽዳት እና ዲስኢንፌክሽን በፊት፣ እንደ የበር ፍሬሞች/መያዣዎች፣ መስታወቶች፣ የመቀመጫ ቀበቶ ቁልፎች፣ የመኪና መሪ፣ ማርሽ መቀየሪያ፣ የምልክት ማድረጊያ ማንሻዎች፣ እና ሌሎች የተሽከርካሪ አካላት ያሉ በደብበኞች እና

ሌሎች አሽከርካሪዎች በተደጋጋሚ የተነኩ ገጽታዎችን ከመንካት ይቆጠቡ።

## ማጽዳት እና ዲስኢንፌክት ማድረግ

- አሽከርካሪዎች ተሽከርካሪዎችን በተደጋጋሚ ሙሉዉን ቀን፣ እና የደንበኛ አገልግሎት መካከል፣ ለማጽዳት እና ዲስኢንፌክት ለማድረግ ሁለገብ እቅድ ሊኖራቸው ይገባል።
- ተሽከርካሪዉ ዉስጥ የዲስኢንፌክታንት መረጫ ወይም የሚጣሉ መጥረጊያዎች እና የሚጣሉ የቆሻሻ ፔስታሎችን ይያዙ። የዲስኢንፌክታንት ምርት መግለጫ ወረቀት ላይ ያሉ መመሪያዎችን ይከተሉ።
- ገጽታዎች በሚታይ መልኩ ከቆሸሹ፣ ከዲስኢንፌክት ማድረግ በፊት በዲቴርጀንት ወይም ሳሙናና ዉሃ መጽዳት አለባቸው።
- በትንሹ፣ በያንዳንዱ ፈረቃ መጀመሪያ እና ማለቂያ ፣ እና የታመሙ ደንበኞችን መጓጓዝ መካከል በተሽከርካሪው ዉስጥ ያሉ በተደጋጋሚ የተነኩ ገጽታዎችን ያጽዱ እና ዲስኢንፌክት ያድርጉ።
- ከደንበኞች መካከል ለማጽዳት እና ዲስኢንፌክት ለማድረግ ለበቂ ጊዜ ይፍቀዱ።
- ስለ ማጽዳት እና ዲስኢንፌክሽን እና COVID-19 የሚያመጣ ቫይረስ ላይ ዉጤታማ የሆኑ ዲስኢንፌክታንቶች ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ፣ የ CDC ድህረገፅን፥ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/organizations/cleaning-disinfection.html ይመልከቱ።

## ለCOVID-19 ተጋላጭነት እቅድ ያዋቅሩ

- ሰራተኛ/አሽከርካሪ ላይ COVID-19 የታየባቸው ጊዜ ዉስጥ እቅድን ያዋቅሩ።
- ለ COVID-19 ተመርምረው ፖዚቲዝ ከሆኑ እና ይህንን መረጃ ለማዉጣት ከመረጡ፣ ሰራተኛ/አሽከርካሪ ማሳወቅ የሚችሉበት በተቋም/ራይድሼር አገልግሎት ቦታ የንክኪ ነጥብን ይለዩ።
- ሰራተኞች/አሽከርካሪ ለCOVID-19 ፖዚቲቭ እንደሆኑ ለተቋም/ራይድሼር አገልግሎት ሪፖርት ለማድረግ ከመረጡ፣ ተቋሙ/ራይድሼር አገልግሎቱ ቀጥሎ ያሉትን ለሠራተኞች ለማጋራት የማሳወቂያ ሂደትን ሊኖራቸው ይገባል፥
  - ስለ COVID-19 ትምህርት፣ የCOVID-19 ምልክቶችን ጨምሮ፣
  - COVID-19 እንዳለበት የተረጋገጠው ሰው ግንኙነቶች መመሪያ ማጣቀሻ በ coronavirus.dc.gov ይገኛል።
- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዉስጥ ስለ COVID-19 ምርመራ አማራጮች ላይ መረጃ ከፈለጉ፣ በ coronavirus.dc.gov/testing ይገኛል
- ተቋማት/ራይድሼር አገልግሎቶች የሚከተሉት ሲከሰቱ DC Health ማሳወቅ አለባቸው፥
  - ሰራተኛ/አሽከርካሪ ለ COVID-19 ተመርምሮ ፖዚቲቭ እንደሆነ ተቋሙን ካሳወቀ (ዉጤቶች ተመልሰው ሳይመጡ በፊት)
    **እንዲሁም**
  - ሰራተኛው/አሽከርካሪው በተደጋጋሚ ከደንበኞች ጋር የሚገናኝ ከሆነ
    ***ወይም***
  - ደንበኛ ለ COVID-19 ተመርምሮ ፖዚቲቭ እንደሆነ ተቋሙን ካሳወቀ

- የ DC Health COVID-19 ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶች ድህረገጽ ላይ dchealth.dc.gov/page/covid-19-reporting-requirements የኦንላይን ቅጽ በማስገባት DC Healthን ያሳዉቁ፥
  - የ ጤና እንክብካቤ-ያልሆነ **ተቋም የ COVID-19 ምክር ቅጽ**ያስገቡ።
- የ DC Health መርማሪ በ48 ሰዓታት ዉስጥ በትክክል ለሁሉም ክትትል ያደርጋል።
  የገቡ ማስታወቂያዎች።

ወረርሽኙ ሲቀየር እነዚህ መመሪያዎች መሻሻላቸውን ይቀጥላሉ። ለወቅታዊ መረጃ እባክዎ coronavirus.dc.gov በመደበኛነት ይጎብኙ።